በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 2!!!

**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

መስከረም ፱ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.



UNABRIDGED • 8 CDs

# ECKHART TOLLE

OPRAH'S Book Club®


# A NEW EARTH

## Awakening to Your Life's Purpose

PENGUIN AUDIO

The #1 *New York Times* Bestselling Author of *The Power of Now*

READ BY THE AUTHOR


THE 6 MILLION-COPY
WORLDWIDE BESTSELLER
A NEW
EARTH
CREATE A BETTER LIFE
ECKHART TOLLE
AUTHOR OF THE POWER OF NOW

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## *የኦፕራ ቡክ ክለብ ምርጫ የሆነው ‹‹A New Earth›› መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲገመገም*

## *1. መግቢያ*

- በቴሌቪዥን ዝግጅትዋ በብዙዎች ዘንድ ታዋቂነትን ያተረፈችው ኦፕራ ዊንፍሬ ‹‹*A New Earth*›› የሚል ርዕስ በተሰጠውና በEckhart Tolle ክርስቲያናዊ መልእክት የሚያስተላልፍ መስሎ የተጻፈውንና ብዙዎችን እያሳተ ወደ ጥፋት የሚያደርሰውን መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ሚዛን እንደሚከተለው በመመርመር ኦርቶዶክሳውያን የተዋሕዶ ተከታዮች ክርስቲያኖች ከዚህና ይህን ከሚመስሉ መጻሕፍት ራሳቸውንና ሌሎችንም እንዲጠብቁ እንመክራለን፡፡
- መጽሐፉ ‹‹እኛነታችንን›› አሻሽሎ ፈጥሮ በተለየ መልኩ የሚያቀርብና የድኅነት ቁልፉ ክርስቶስ ሳይሆን ‹‹ኅሊናችን›› እንደሆነ በዘመናችን የሚገጥሙን ችግሮች ምንጫቸው ኃጢአት ሳይሆን ነገሮች የተመለከትንበት አቅጣጫ የተሳሳተ መሆን ነው የሚሉ ቁልፍ መልእክቶችን ያስተላልፋል፡፡
- ጥንታዊው የምስራቃውያን ‹‹ሃይማኖታዊ›› አስተሳሰብ በዘመናዊው የምዕራባውያን ልብስ ተሸፍኖ የቀረበ ‹‹የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ - መንፈሳዊነት›› መጽሐፍ ነው፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## *2. የመጽሐፉ ቁልፍ መልእክቶች*

- ሰዎች ከንቱ ከሆነ የሕይወት ኃይል ተገኝተዋል፡፡
- ሰዎች ከሰማይና ከምድር የሕይወት ኃይል ጋር አንድ እንደሆንን ማወቅ የሚያስችል አቅም ወይም ጉልበት አለን፡፡
- የሰው ልጆች ሁሉ የተፈጠሩበት ዋና ዓላማ ‹‹ተፈጥሮአቸው›› የአንድ ሕይወት ኃይል አካል መሆኑን እንዲያውቁ ነው፡፡
- በርካታ ሕዝቦች ስለተፈጥሮአቸው ጥልቅ የሆነ ግንዛቤ የላቸውም፣ ስለራሳቸውም ባለፈው ትናንት ላይ ተመስርተው ዘወትር ራሳቸውን በመፈለግ መርካት የማይታይበት የተሳሳተ ሥዕል (መረዳት) አላቸው፡፡
- በተጠቀሰው መንገድ የራሳችንን ትክክለኛ ማንነት አለማወቃችን ዓለምንና የሰውን ዘር ወደ ጥፋት ጫፍ አድርሷል፡፡
- ይህን ጥፋት ለማስቀረት ከቅዠት ወደ ኅሊናችን መመለስ ያስፈልገናል፡፡
- ኅሊናም እንዲኖረን በ‹‹ዛሬ›› ውስጥ መኖር አለብን፤ ይህን ካደረግንም አዲስ የዓለም ሥርዓት ይፈጠራል እርስዋም ‹‹አዲሲቱ ምድር›› ናት.. የሚሉ ናቸው፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## *3. መጽሐፉ ስለምን ታዋቂነትን አገኘ?*

***በመቻቻል አስተሳሰቦቹ***

- *መጽሐፉ በዙሪያችን ያለው ዓለም ክርስትናን እውተኛ ሌሎች ‹‹ሃይማኖቶችን›› ሐሰተኛ አድርጎ ማመን አለመቻቻልና አስከፊም እንደሆነ አድጎ ይሰብካል፡፡*
- *በዚህም የመጽሐፍ አቀራረብ የሚወደደው ክርስትና የሁሉንም ‹‹ሃይማኖቶች›› እምነትና ባሕል እንዲቀበልና እንዲከተል ይገደዳል፡፡*

***የኦፕራ ዊኒፍሬ ድጋፍ***

- *ኦፕራ መጽሐፉን በመረጃ መረብዋ ሴሚናር አማካይነት ለዚህ መጽሐፍ ከፍተኛ ድጋፍዋን ሰጥታለች፡፡ ለዚህም ተግባርዋ ‹‹እስካሁን ከሠራችው የሚልቅ አስደናቂ ሥራዋ ነው፡፡›› ተብሎ ከፍ ያለ ሙገሳ አግኝታበታለች፡፡*
- *በመጀመሪያው የመረጃ መረብ ሴሚናር ወቅት የመጽሐፉን መልእክቶች ካደገችበት ‹‹ክርስቲያናዊ›› ሁኔታ አንጻር እስዴት እንደምትመለከተው ስትጠየቅ ‹‹በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከተመሠረተው ትምህርተ ሃይማኖት ‹ሳጥን› ውስጥ የወጣሁት ከ20 ዓመት ዕድሜዬ ጀምሮ ነው፡፡ ለዚህም ክስተት ምክንያት የሆነኝ በ20 ዓመት ዕድሜዬ ‹እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው› ብሎ ካስተማረኝ መምህር የተማርኩት ትምህርት ነው፡፡ ቀናተኛውን ሳይሆን የፍቅርን አምላክ ማመን ፈለግሁ… ከክርስትና ይልቅ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ ብዙ መንገዶች አሉ ብዬ የማምን ክርስቲያን ነኝ፡፡›› በማለት ምላሽዋን ሰጥታለች፡፡*

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## *4. መጽሐፉ አደገኛ የሚሆነው ስለምንድር ነው?*

**ግማሽ እውነታ የያዘ መጽሐፍ በመሆኑ**

- መጽሐፉ የሰው ልጆች የሚገጥሙአቸውን ቁጣን፣ ሐዘንን ሌሎቹንም አስመልክቶ ችግሮቹን ሊፈቱ የሚችሉበትን አንዳንድ እውነታዎች ይጠቁማል፡፡ ለምሳሌ ብዙ ሕማምና መከራን ወደዚህ ዓለም ያመጣው ሥጋችን ነው፣ በሁኔታዎች ውስጥ በሐዘን ለመዋጥ የምንገደደው አእምሮአችና ባለፈው ጉዳትና በሚመጣው ፍርሐት (ስጋት) ውስጥ ስለሚዘፈቅ ነው… የሚሉ ሐሳቦቹ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን መጠቀሙ**

- እንደ በርካታዎቹ ሐሰተኞች ነቢያት ሰይጣናዊ ሥራዎቻቸውን ሐሰተኛ ከሆነው ክርስቲያናዊ ሐሰት ጋር ቀላቅለው ያቀርባሉ፡፡ ‹‹እውነተኛ ክርስትና›› ከፍልስፍና ጋር ጠብ የለውም ይስማማል ለማለት ጌታችን በመዋዕለለ ሥጋዌው ካስተማረው ትምህርትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችንን በመጽሐፉ ውስጥ አልፎ አልፎ ጠብ አድርገው ማቅረቡ መጽሐፉን አደገኛ ያደርገዋል፡፡ ይህ መጽሐፍ 25 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና ማገናዘቢያዎች አሉት፡፡

# <u>ተጠበቁ - ክፍል 2</u>

## *5. መልእክቶቹ ሲፈተሹ*

- ስለ እግዚአብሔር
  - <u>*መጽሐፉ*</u>
    - በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው እግዚአብሔር ከሰው የሆነው የሕይወት ኃይል ነጸብራቅ ነው፤ ሁሉ ከእግዚአብሔር እግዚአብሔርም ከሁሉም ተገኝቷልና ሁሉም ቁሳዊ ነገሮች ከመንፈሳዊው የሕይወት ኃይል ጋር ወደ መተባበር መመለስ ያስፈልጋቸዋል።
  - <u>*የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ*</u>
    - እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ እንጂ የሰማይና የምድር አካል አይደለም። <u>*ዘፍጥ 1፡1።*</u> እግዚአብሔር አንድም ሦስትም - ሥላሴ ነው። <u>*ቀዳ ዮሐ 5፡7።*</u>
    - እግዚአብሔር ራሱን ለፍጥረቱ በፍጥረቱ <u>*መዝ 19፡1*</u>፣ በቅዱሳት መጻሕፍቱ <u>*ዮሐ 5፡39*</u> እንዲሁም በአንዱ ልጁ በጌታችን በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ገልጧል። <u>*ዕብ 1፡1-2።*</u>

# <u>ተጠበቁ - ክፍል 2</u>

## *5. መልእክቶቹ ሲፈተሹ*

- ስለ ሰው ልጅ ተፈጥሮ
  - <u>*መጽሐፉ*</u>
    - ሰዎች ስለ ተፈጥሮአቸው እና ከአንዱ የሕይወት ኃይል ጋር አንድ መሆናቸውን ማወቅ ይችላሉ፡፡
    - እኛ ብቸኛ ሳንሆን የአንድ ሕይወት ኃይል ቁሳዊ መገለጫዎች ነን፡፡
    - የመኖራችንም ትርጉሙ የአንዱ ሕይወት ኃይል በዚህ ዓለም እንዲታወቅ ነው፡፡ ‹‹በዚህ ዓለም የመኖራችን ምስጢሩ ያን ኃይል ወደዚህ ዓለም ለማምጣት ነው፡፡›› <u>ገጽ 78፡፡</u>
    - ‹‹እውነት ከአንተ ተነጥሉ የሚታይ አይደለም፤ አንተ እውነት ነህና፤ በሌላ ቦታ ስትመለከተው ልትሳሳት ትችላለህ፤ ዋናው ነገር አንተ እውነት መሆንህን ማወቅ ነው፡፡›› <u>ገጽ 71፡፡</u>
    - መጽሐፉ እኛ እውነት መሆናችንን ለማስረዳት ኢየሱስ ‹‹እኔ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት ነኝ›› ብሏል ይለናል፡፡ በአባባሉም ጌታችን ‹‹በእኔ ካልሆነ ማንም ወደ አባት ሊደርስ አይችልም›› ያለውን ግን ይዘለዋል፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## 5. *መልእክቶቹ ሲፈተሹ*

- ስለ ሰው ልጅ ተፈጥሮ
  - <u>*የመጽሐፍ ቅዱስ መልሶች*</u>
    - ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል በራሱ በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል።
    - የለበስነው ምድራዊ አካላችን ጊዜያዊ ሲሆን ነፍሳችን ግን ዘላለማዊት ናት። <u>*መክ 12፡7።*</u> በርግጥ እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር የተዘጋጀልንን ዓላማ የመፈጸም ኃላፊነት ያለብን ስንሆን ይህኑ ለማሳካትም ሆነ ዕድላችን እንዲሰምር ከእግዚአብሔር ጋር መኖር አለብን። <u>*ዮሐ 5፡29፣ ማቴ 7፡21-23።*</u>
    - ጌታችን እንደቃሉ የምንኖር ከሆነ ‹‹እውነትን እንደምናውቅ›› ነገረን እንጂ ‹‹እውነት ትሆናላችሁ›› አላለንም። ዮሐ 8፡31-32።
- ኃጢአትና ክፋት
  - <u>*የመጽሐፉ መልእክት*</u>
    - ኃጢአት ሰው የራሱን ኅልውና እንዳይረዳ የሚገድበው በሽታ ነው። እኛ አካላችንን ወይም አሳባችንን ስላልሆንን ስለምንሠራው ኃጢአት ተጠያቂ አይደለንም። ‹‹በዓለም ውስጥ ለኃጢአት ተጠያቂ የሚሆነው አለማወቅ ነው፤ ሰዎች በሕመም በተያዘ ሰውነት ለሚሠሩት ኃጢአት ተጠያቂ አይደሉም።›› <u>*ገጽ 163።*</u>

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## *5. መልእክቶቹ ሲፈተሹ*

- ኃጢአትና ክፋት
  - ***<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ምላሽ</u>***
    - በኃጢአት የተነሳ የሰው ወገኖች ሁሉ (ከእመቤታችን በቀር) ውጤቱን ዕዳውን ተሸክመን እንወለዳለን፡፡ ይህም ክፋን የማወቅ ዕውቀት የተገለጠው ከእግዚአብሔር ስንለይ ነው፡፡ ‹‹ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል›› ***<u>ሮሜ 3፡23</u>***፣ ‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ ›› ***<u>ሮሜ 6፡23፡፡</u>***
- ድኅነት
  - ***<u>የመጽሐፉ መልእክት</u>***
    - *መልካም ለመሆን በመጣጣር መልካም አትሆንም፣ በአንተ ውስጥ መልካምነት ግን ፈልገውና ከውስጥህ እንዲመነጭ ፍቀድለት፤ ይህም ሊሳካ የሚችለው መሠረታዊ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ስታደርግ ነው፡፡›› ገጽ 13፡፡*
    - ስንሞት በሰማይና በምድር ባለው የሕይወት ኃይል ውስጥ እንደ አንድ ልዩ ፍጥረት ሆነን እንኖራለን፡፡
    - የምናምነው ምንም ይሁን ምን በምድር በሚኖረው ሕይወታችን ሁላችን አንድ የጋራ ግብ አለን፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## 5. መልእክቶቹ ሲፈተሹ

- ድኅነት
  - <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ምላሽ</u>
    - ሰው መልካም ሆኖ የተፈጠረ ቢሆንም በበደል የተነሳ ግን ጸጋውን ተገፎአል፡፡ *<u>ሮሜ 7፡15-24፡፡</u>*
    - ሁላችንም በመንፈስ ሕያው ነን፡፡ *<u>ዮሐ 5፡28-29፡፡</u>* በሥጋ ከሞትን በኋላ መንፈሳዊ ኑሮ በወዲያኛው ዓለም ይጠብቀናል፡፡ የወደፊት ዕድላችን ግባችንም የሚወሰነው አሁን ከጌታችን ጋር ባለን ግኑኝነትና ቃሉን ለመፈጸም እንደመፍቀዳችን መጠን ነው፡፡ ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም፡፡ ›› *<u>ዮሐ 5፡24፡፡</u>*
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
  - <u>የመጽሐፉ መልእክት</u>
    - ጸሐፊው ጌታችንን ‹‹የበራለት ሰው ነው፡፡ ይህን ብሩህነቱን ይዞ ቡድሃንና ይህን ሓሳብ ለሕዝብና ለማኅበረሰቡ የሚያስተላልፉ ሰዎችን ተቀላቀላቀለ›› ይለዋል፡፡
    - ጸሐፊው በመቀጠልም ኢየሱስ ‹‹ተራ ሰው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም፤ ልዩ ያደረገው ነገር እርሱ የአንድ ሕይወት ኃይል አካል መሆኑን ማወቁ ነው፡፡›› ይለዋል፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 2

## 5. *መልእክቶቹ ሲፈተሹ*

- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
  - *የመጽሐፍ ቅዱስ ምላሽ*
    - ጌታችን አምላካችን ‹‹እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።›› ብሎናል፡፡ *ዮሐ 14፡6፡፡*
    - ቅዱስ ጴጥሮስም ስለ ጌታችን ሲናገር ‹‹መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፡፡ ›› *የሐዋ 4፡12፡፡*
    - ቅዱስ ዮሐንስም ‹‹በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ›› ብሎናል፡፡ *ዮሐ 1፡1፡፡*
- ይህ መጽሐፍ በዘመናችን ዓለም እየተዋወቀችው የምትገኘው እንግዳ የአዲሱ ዘመን መንፈሳዊነት አንድ ገጽታ ነው፡፡
- ይህም ውጊያ ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እንግዳ ስላልሆነ እነዚህን የሰይጣንን መውጊያዎች *ገላ ቆሮ 2፡11፡፡* በጽንዓትና በማይናወጽ እምነት ሆነን መቋቋም ይገባናል፡፡ *ቀዳ ቆሮ 15፡58፡፡*
- ቅዱስ ጳውሎስም በመልእክት ‹‹እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ፡፡››*ቆላ 2፡8፡፡* እንዳለን ከሐሰት መምህራንና ትምህርቶች በእውነተኛይቱ ሃይማኖትና በምግባር ሆነን እንጠበቅ፡፡

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org